# እንኳን ከዘመነ ማቴዎስ ወደዘመነ ማርቆስ በሰላም ያሸጋገራችሁ

ከጌታቸው ኃይሌ

ሃይማኖታችን እንደሚያስተምረን፥ ዘመን መጀመሪያም መጨረሻም የለውም፡፡ አበው የሚያስተምሩት "ዓለም ታልፋለች" እያሉ እንጂ ዘመን ያልፋል አይሉም፡፡ ዘመን ዓለም ከመፈጠሩ በፊት ነበረ፤ ዓለም ካለፈ በኋላም ይኖራል፡፡ በዚህ አስተያየት፥ እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ ፈጠረው ከማለት ይልቅ "ዘመንን በአምሳሉ ፈጠረው" ቢባል ለመረዳት የበለጠ ይቀልላል፡፡ በዓሥራ አምስተኛው ምእት ዓመት አባ ገማልየልና አባ ዘሚካኤል ከአዬ ዘርአ ያዕቆብ ጋር ሲከራከሩ ቅዱስ ዮሐንስን እንደጠቀሱት፥ (የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ 1፥ ቍጥር 18) "እግዚአብሔርን ያየው ፈጽሞ የለም"ና መልኩ ሰው ይመስላል ለማለት ማስረጃ የለንም፡፡ "በአምሳሉና በአርአያው ፈጠረው" ማለት ማሰብ የሚችል አድርጎ ፈጠረው ማለት ሳይሆን አይቀርም፡፡ ዘመን ግን መጀመሪያና መጨረሻ ስለሌለው "ዘመንን በአምሳሉ ፈጠረው" ብንል ህርጥቅና (ክሕደት) አይሆንም፡፡

ዘመን መጀመሪያ ስለሌለው ማንኛውንም አንዱን ቀን የዘመን መጀመሪያ ልናደርገው እንችላለን፡፡ ግን በዚያ ጀምሮ ያለውን ዘመን በምን እየለካን አንድ ሁለት እያልን እንቍጠረው? ፀሐይን አንድ መቍጠሪያ አደረጓት፤ መጀመሪያ ከወጣችበት ጊዜ አንሥቶ እንደገና እስከምትወጣበት ድረስ ያለውን ዘመን አንድ ዕለት አሉት፡፡ "አንድ ዕለት" የሚባለው የፀሐይዋ ብርሃን የሚታይበት እና የማይታይበት ዘመን ተደምሮ ነው፡፡ የፀሐይዋ ብርሃን የሚታይበትን በግዕዝ መዓልት፥ በአማርኛ ቀን አሉት፤ የፀሐይዋ ብርሃን የማይታይበትን (ጨለማውን) በግዕዝም በአማርኛም ሌሊት አሉት፡፡

ፀሐይ ጥሩ መለኪያ ነች፤ ዕለቱን ለመቍጠር ትጠቅማለች፡፡ ግን ዕለታት የሚጠቃለሉበት መቍጠሪያ ያስፈልጋል፡፡ ካልተገኘ ገንዘብን በአንድ ብር ኖት እንደመቍጠር ይሆናል፡፡ የአምስት፥ የዓሥር፥ የኀምሳ፥ የመቶ ብር ኖት እንደሚያስፈልግ ሁሉ ቀኖችም ተጠቃልለው የሚቈጠሩበት ዘዴ አስፈለገ፡፡ ለዚህም አንድ ሰው-ሠራሽና አንድ እግዜር-ሠራሽ መለኪያ አመጡ፡፡ ሰው-ሠራሹን "ሳምንት" ሲሉት፥ እግዜር-ሠራሹን <u>ወር(ኅ)</u> አሉት፡፡ ሳምንት ሰባት ቀን ነው፤ ሰው-ሠራሽ ያልኩት ቢፈልጉ ዓሥር ቀን ቢያደርጉትም እምቢ አይልም ነበር ለማለት ነው፡፡ ወርኅ የግዕዝ ቃል ነው፤ ጨረቃ ማለት ነው፡፡ ፀሐይን የዕለት መለኪያ ጨረቃን የሐያ ዘጠኝ/የሠላሳ ቀን መለኪያ አደረጓቸው፡፡ ሌላው ለወር መለኪያ ሞከር አድርገው የተውት እግዜር-ሠራሽ መለኪያ በየወሩ የሚመጣው የሴቶች አበባ ነው፡፡ ሦስተኛው ዘመን ዓመት ይባላል፡፡ ዕለትና ወር(ኅ) መለኪያ ሲኖራቸው ዓመት እንደሳምንት መለኪያ የለውም፡፡ ግን ምልክቶች ስላሉት ከሳምንት ይሻላል፡፡ አንድ ክረምትና አንድ በጋ አንድ ዓመት ይወጣቸዋል፡፡

ዕለት፥ ሳምንት፥ ወር፥ ዓመት፥ እየተመላለሱ ስለሚመጡ መጨረሻ አልባውን ዘመን ለመለኪያ ጠቅመዋል፡፡ ምልሳቸውም ስም ወጥቶለታል፤ ዓውድ ይባላል፡፡ የሁሉንም ጥቅም እዚህ ለመጻፍ ባይመችም፥ ዓውዶቹ እነማን እንደሆኑ ለማሳየት ያህል ልዘርዝራቸው፤
(1) ዓውደ ዕለት (24 ሰዓት)፥
(2) ዓውደ ወርኅ (29/30 ቀን)፥
(3) ዓውደ ዓመት (365 ቀን ከ5 ሰዓት ከ48 ደቂቃ ከ46 ዳግሚት)፥
(4) ዓውደ ጳጕሜን (በየ4 ዓመት ዓመቱ 366 ቀን የሚሆንበት)፥
(5) ዓውደ አበቅቴ (19 ዓመት፥
(6) ዓውደ ፀሐይ (28 ዓመት)፥
(7) ዓውደ ማኅተም (76 ዓመት)፥
(8) ዓውደ ቀመር (532 ዓመት)፡፡

ሰው-ሠራሽ ስለሆነ ነው እንጂ ሳምንትም ተመሳሳሽ ስለሆነ ዓውደ ሳምንት ቢሉት አያስቀይምበትም፡፡ አልተባለም እንጂ፥ ዓውደ ጳጕሜንም ዓውደ ወንጌላውያን ቢሉት ያስኬዳል፡፡ በውስጡ ያሉት አራቱ ዓመቶች ለወንጌላውያን ተሰጥተው በማቴዎስ፥ በማርቆስ፥ በሉቃስ፥ በዮሐንስ ስም ይጠራሉ፡፡

ክርስቲያኖች ባሕረ ሐሳብን ለማውጣት የተገደዱት ከአይሁድ ጋር ባላቸው ዝምድናና ጠብ ምክንያት ነው፡፡ በዝምድናው ልጀምርና የአይሁድ ፋሲካ (ፍሥሕ) የክርስቶስ መሥዋዕትነት ትንቢት ነው፡፡ ክርስቶስ የተሠዋው (የተሰቀለው) የአይሁድ ፋሲካ (ፍሥሕ) እንደተበላ ነው፡፡ ያን ዕለት ትንቢቱ ተፈጸመ፡፡ ክርስቶስ የተሠዋበትንና ከሙታን ተለይቶ የተነሣበትን ለማስታወስ ሁል ጊዜ የአይሁድ ፋሲካ (ፍሥሕ) በሚውልበት ቀን መሆን አለበት፡፡ ግን ያንን ቀን ለመጠበቅ የሚያስቸግሩ ሁለት ነገሮች አጋጠሙ፤ አንደኛው ችግር፥ ክርስቲያኖች ዘመን የሚቈጥሩት በፀሐይ ሲሆን አይሁድ የሚቈጥሩት በጨረቃ (በወርኀ) ነው፡፡ “በፀሐይ መቍጠር” ማለት “በዕለት መቍጠር” ማለት ነው፤ ፀሐይ የምትሰጠውን ዕለት ቈጥሮ 365 ቀን ከ5 ሰዓት ከ48 ደቂቃ ከ46 ዳግሚት ሲሆን አንድ ዓመት ሆነ ማለት ነው፡፡ አይሁድ ዓመታቸውን የሚቈጥሩት በጨረቃ (በወርኀ) ስለሆነ ዓመታቸው አጭር (354 ዕለት) ከመሆኑም በላይ ፋሲካቸው ዓመታቸውን በፀሐይ ለሚቈጥሩ ሁል ጊዜም በዓመቱ ውስጥ በዚያው ቀን አይውልም፤ ይንፏቀቅባቸዋል፡፡

ሁለተኛው ችግር የተፈጠረው አይሁድና ክርስቲያኖች የተጣሉና የተኳረፉ ዕለት ነው፡፡ ክርስትና ከይሁዳ ሃይማኖት አፈንግጦ ሲወጣ አይሁድ ተቆጥተው አፈንጋጮቹን (ክርስቲያኖቹን) አሳደዋቸው ነበረ፡፡ ስደትና ጭቆና በዝቶባቸው ስለነበረ፥ የፋሲካ በዓላቻውን ከነሱ ጋር እንዳያከብሩ ወሰኑ፡፡ ግን ዕለተ በዓሉ ብዙ እንዳይርቅ፥ ሁለተኛም ምን ጊዜም ቢሆን ስቅለት ዓርብን፥ ትንሣኤ እሑድን እንዳይለቁ አብረው ወሰኑ፡፡

“ዘመን መጀመሪያ ስለሌለው ማንኛውንም አንዱን ቀን የዘመን መጀመሪያ ልናደርገው እንችላለን” ብያለሁ፡፡ እውነትም የሆነው ይህ ነው፡፡ ሮማውያን ከተማቸው የተቈረቈረችበትን ዓመት የዘመን ቈጠራ መጀመሪያ አድርገውት ነበር፡፡ ግሪኮች እስክንድር የገነነበትን ዓመት የዘመን መቍጠሪያ አድርገውት ነበር፡፡ ሙስሊሞች ነቢዩ መሐመድና ሙስሊሞች ከመካ ከተማ የተሰደዱበትን ዓመት የዘመን ቈጠራቸው መጀመሪያ አድርገውታል፡፡ ይህ የሚያሳየው ሕዝብ ሁሉ ዘመን ቈጠራን እንደባህሉ እንደታሪኩ የሚይዘው መሆኑን ነው፡፡ ስለዚህ “የኛ የዘመን ቈጠራ ከእነሱ የዘመን ቈጠራ ለምን ይለያል?” ማለት “የኛ ባህል ከእነሱ ባህል ለምን ይለያል?” እንደማለት ነው፡፡

መልሴ ልክ ቢሆንም፥ ጠያቂን መቶ በመቶ አያረካውም፡፡ በኛ ዓመተ ምሕረት (ዓ.ም.) በምዕራባውያን ዓመተ እግዚእ (ዓ.እ.= Anno Domini=AD.) የሚባለው የዘመን ቈጠራ በሁለቱም ዘንድ ከክርስቶስ ልደት ጋር የተያያዘ ሆኖ ሳለ፥ ለምን ተለያየን? ይኸም ከሞላ ጎደል ከባህል ጋር የተያያዘ ነው፡፡ እኛና ምዕራባውያን ዘመን ቈጠራ የጀመርነው ከክርስቶስ መወለድ በፊት በየባህላችን ነበር፡፡ በየባህላችን ከሆነ ቀደም ብለን እንደየባህላችን ተለያይተን ነበር ማለት ነው፡፡ የኛ የዘመን ቈጠራ የሚነሣው እግዚአብሔር ለአዳም ከሰጠው ተስፋ ነው፡፡ ተስፋው፥ አዳም በጥፋቱ ከገነት በመባረሩ በመሪር ሐዘን፥ በለቅሶ ሲጸጸት ጊዜ፥ ከ5500 ዓመት በኋላ ከልጅ ልጅህ (ከቅድስት ማርያም ማለት ነው) ተወልጄ ጥፋትክን ተሸክሜ፥ እዳህን በአንተ ፈንታ ከፍየልህ አድንነለሁ የሚል ነበረ፡፡ ልክ 5500ው ዓመት አልቆ 5501 ዓመተ ዓለም በተጀመረበት ዓመት በታኅሣሥ 29 ክርስቶስ ተወለደ፡፡ ክርስቲያኖች ዓመተ ምሕረት (ዓ.ም.) የሚሉት ክርስቶስ ከተወለደበት ዓመት ጀምሮ ያለውን እንጂ ከተወለደበት ቀን ጀምሮ ያለውን አይደለም፡፡ ክርስቶስ የተወለደበት ዓመት የጀመረው በባህላችን መሠረት መስከረም ላይ ሲሆን፥ ክርስቶስ የተወለደው ታኅሣሥ 29 ቀን፥ 5501 ዓመተ ዓለም፥ ወይም ታኅሣሥ 29 ቀን፥ 1 ዓመተ ምሕረት ላይ ነው፡፡

ክርስቶስ በተወለደበት ዘመን የነበረው የምዕራባውያን  የዘመን ቈጠራ የሚነሣው ከሮም ከተማ ምሥረታ መሆኑን እናስታውሳለን፡፡ ዓመታቸው የሚጀምረው በጃኑዋሪ ነው፡፡ እነሱም ክርስቶስ በታኅሣሥ ወር እንደተወለደ ያምናሉ፡፡ ሆኖም ቈጠራቸውን ወደ ዓመተ እግዚእ (ዓ.እ.= Anno Domini = A.D.) ሲለውጡ ጃኑዋሪን የዘመን መለወጫ መሆኑን አላስቀሩም፡፡ እኛ መስከረምን እንዳልለቀቅን እነሱም ጃኑዋሪን አልለቀቁም፡፡ በነሱ ባህል ክርስቶስ የተወለደው ዲሴምበር 25 ቀን፥ 1 ቅድመ ክርስቶስ (ቅ.ክ.) ላይ ነው፡፡

እዚህ ስንደርስ ሁላችንም ክርስቲያኖች ሆነን ሳለ፥ ክርስቶስ በተወለደበት ቀንና ዓመት አለመስማማታችንን እንገነዘባለን፡፡ ጊዜውን (ቀኑንና ዓመቱን) የየራሳችን አበው ገምተው ሰጡን እንጂ፥ ክርስቶስ የተወለደበት ቀንና ዓመት የትም ቦታ ተመዝግቦ አልተገኘም፡፡ ቀን የተወሰነልን በዓሉን እንድናከብር ነው እንጂ ትክክለኛው ቀን ሆኖ ለታሪክ አይደለም፡፡ ምዕራባውያን ለክርስቶስ ልደት በተለይ ዲሴምበር 25 ቀንን የመረጡት የአረመኔዎች (የአሕዛብ) በዓል የሚከበርበት ስለነበረ እሱን ለመለወጥ ወይም ለመደምሰስ መሆኑ ይተረካል፡፡ በኋላ የተነሡ ተመራማሪዎች እንደሚሉት ከሆነ፥ በግምት የተደረሰበት የኛ ዓመት በ14 ዓመት፥ የነሱ ዓመት በ7 ዓመት ወደኋላ ቀርቷል፡፡ በተመራማሪዎቹ አስተሳሰብ ክርስቶስ የተወለደው ቅድመ ክርስቶስ (Before Christ, BC) ተብሎ በሚቈጠረው ዘመን ነው፡፡

በእኛና በነሱ መካከል አቈጣጠር የ7/8 ዓመት ልዩነት አለ፡፡ ብዙ ሰዎች ይኸንን ልዩነት የጁሊያን ካሌንደርና የግሪጎርያን ካሌንደር ልዩነት ነው ይላሉ፤ ተሳስተዋል፡፡ ይህ የሰባት/የስምንት ዓመት ልዩነት ከባህል መለያየት የመጣ ልዩነት ነው እንጂ፥ የጁሊያን ካሌንደርና የግሪጎርያን ካሌንደር መለያየት ያመጣው ልዩነት አይደለም፡፡ የጁሊያን ካሌንደርና የግሪጎርያን ካሌንደር ልዩነት የሚባለው ወር ሲጀምሩ በአንድ ቀን በመጀመር ፈንታ በ11 ቀን ተለያይተው ስለሚጀምሩ ነው፡፡ ለምሳሌ እኛ ዛሬ መስከረም 1 ስንል እነሱ ሴፕተምበር 11 ይላሉ፡፡ ወይ እነሱ ሴፕተምበር 1 ወይ እኛ መስከረም 11 ማለት ነበረብን/ነበረባቸው፡፡ እንደእውነቱ ከሆነ እኛ መስከረም 11 ማለት ነበረብን፡፡ መልሴን ከማብራራቴ በፊት አንድ ተረት ብጤ ምሳሌ ልመስል፡፡

አንድ መሀንዲስ 365 ኪሎ ሜትር፥ ከ99.89 ሜትር እየለካህ ምልክት አድርግ ተብሎ ይታዘዛል፡፡ መሀንዲሱ በእጁ ያለው መለኪያ አንድ ኪሎሜትር ርዝመት ያለው ቀላድ ብቻ ስለሆነ፥ “ልዩነት ለማያመጡ ዋጋ ለሌላቸው ሚሊሜትር ስል ሜትር  ፍለጋ ከመሄድ” ይልና 366 ኪሎሜትር እየለካ ምልክት አደረገ፡፡  በኋላ ተቈጣጣሪ መጥቶ ቢመረምር እንዲለካ ከተሰጠው መሬት 11 ኪሎሜትር አልፎ ተገኘ፡፡ ከቀሪው መሬት 11 ኪሎሜትር አጕደለ፡፡ 11ዱንም ወደሚቀጥለው መሬት አስተላለፉት፡፡

ዓመት በድፍን ቀን አይቈጠርም፡፡ የኒው ዮርክ የኮረንቲ ኳስ አዲሱን ዓመት ለማብሠር ልክ እኩለ ሌሊት ሲሆን ወደታች የሚወርደው የችግር ነው፡፡ አንድ ዓመት ሞላ ወይም አለፈ የሚባለው 365 ቀን ከ5 ሰዓት ከ48 ደቂቃ ከ46 ዳግሚት ሲያልፉ ነው፡፡ እውነተኛውን የዘመን መለወጫ ለማክበር የሚፈልግ 46ተኛዋ ዳግሚት (second) ሳትቀር ስትሞላ ነው፡፡ ዓመቱ 365 ቀን ከ5 ሰዓት ከ48 ደቂቃ ከ46 ዳግሚት መሆኑን ቄሳር ዩሊዩስ በ46 ቅድመ ክርስቶስ (ቅ.ክ.) በምርምር ደርሶበት እስከዚያ ዘመን ይጠቀሙበት የነበረውን ባሕረ ሐሳብ በብዙ አስተካከለው፤ ግን ጉዳት አያመጠም ብሎ፥ ዓመቱን 365 ቀን ከ6 ሰዓት አደረገው፡፡ ምን ማለት ነው? አሮጌው ዓመት ሞልቶ፥ አዲሱ ዓመት 11 ደቂቃ ከ14 ዳግሚት ከሆነው በኋላ አሁን ገና አሮጌው ዓመት ሞልቶ፥ አዲሱ ዓመት ተጀመረ እንድንል አደረገ፡፡ እንግዴህ ዘንድር ዓመት ሳንለውጥ 11 ደቂቃ ከ14 ዳግሚት ወደኋላ ቀረን እንበል፡፡ የሚመጣው ዓመትስ? ያንጊዜማ የባሰ ነው የሚሆነው፡፡ ባለፈው ስሕተት ላይ የዘንድሮውን ስሕተት ጨምረን 22 ደቂቃ ከ14 ዳግሚት ወደኋላ ልንቀር ነው፡፡ ዓመት በጨመረ ቍጥር በጥቂት ደቂቃዎችም ቢሆን የዓመቱ መጀመሪያ እየራቀ ይሄዳል፡፡

ዩልዩስ ቄሳር በ46 ቅ.ክ. ያደረገውን የዘመን ቈጠራ እድሳት ፖፕ ግሬጎሪ በ1528 ዓመተ እግዚእ (አ.እ.) ሲመረምረው ከዘመን ብዛት የዓመቱን መጀመሪያ በ11 ቀን ወደኋላ እንዳስቀረው ተገነዘበ፤ አረመው። የኛ ወር የሚጀምረው የምዕራባውያን ወር በጀመረ በ11 ቀኑ መሆኑ ስለዚህ ነው። ፖፕ ግሬጎሪ የቄሳር ዩልዩን ካሌንደር የጨመራቸውን 11 ቀኖች ቈርጦ ጣላቸው እንጂ ራሱን አቈጣጠሩን አላረመውም። ስለዚህ 11ዱ ደቂቃና 14ቱ ዳግሚት አሁንም በመከማቸት ላይ ናቸው። ተከማችተው ከጊዜ ብዛት ብዙ ቀናት ሲወጣቸው አንድ ሌላ ግሬጎሪ ወይም አንድ ኢትዮጵያዊ ሊቅ ተነሥቶ፥ ያስተካክላቸው ይሆናል።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን እንደምታስተምረው፥ ዓለም ሲያልፍ፥ የዘመን መለኪያዎች ፀሐይና ጨረቃም አብረው ያልፋሉ። ከዚያ በኋላ ለጻድቃኑ ብርሃን የሚሰጣቸው ከአምላክ ዘንድ የሚመጣ ጸዳል ነው። ጸዳሉ ከጭለማ ጋር ስለማይፈራረቅ ጻድቃኑ የሚኖሩት መጨረሻ በሌለው በአንድ ዕለት/ቀን ብቻ ነው። ያ አንድ ዕለት አምላክን እያመሰገኑ የሚያርፉበት ቀን ስለሆነ "ሰንበት" ይባላል። ሰንበት የተባለው "እግዚአብሔር ዓለምንና በውስጧ ያሉትን ሠርቶ ያረፈበት ቀን "ሰንበት" ስለተባለ ነው። "እግዚአብሔር ያረፈው ቅዳሜ እንጂ በሰንበት አይደለም" የሚል ብልህ ሰው ካለ፥ "ቅዳሜ" የሚለው ቃል ከስም ተቈርጦ የቀረ ቅጽል እንጂ ስም አይደለም። ባይቈረጥ ኖሮ ሙሉው ስያሜ እንደዱሮው "**ቀዳሚት ሰንበት**" ይሆን ነበር። "ቀዳሚት ሰንበት" ማለት "የመጀመሪያዋ ሰንበት" ማለት ነው። ለቅዳሜ ይህ ስም የወጣላት ክርስቶስ ከሙታን የተነሣባት እሑድ "ዳግሚት ሰንበት" (ሁለተኛዋ ሰንበት) ወይም "**ደኃሪት ሰንበት**" (የኋለኛዋ ሰንበት) እንድትባል የተወሰነ ጊዜ ነው።

"ቀዳሚት ሰንበት" እና "ደኃሪት ሰንበት" እኩል የሚከበሩት በእኛ ዘንድ ብቻ ነው እንጂ በሌሎቹ ክርስቲያኖች ዘንድማ "ቀዳሚት ሰንበት" በ"ደኃሪት ሰንበት" ተተክታ ተሽራለች። ፍትሐ ነገሥቱም ቅዳሜን እንደእይሁድ አታክብሯት ቢለንም እስከቅርብ ጊዜ ድረስ የሚሰማው አላገኘም ነበር። ዓለም ከአለፈ በኋላ የምትመጣዋ ዘላለማዊቷ ሰንበት ሁለቱን ሰንበቶች፥ ማለት ቅዳሜንና እሑድን፥ (ቀዳሚት ሰንበትንና ደኃሪት ሰንበትን) ስለምትወክላቸውና ስለምትበልጣቸውም "**ሰንበተ ሰንበታት**" (የሰንበቶች ሰንበት) ትባላለች። በሰንበተ ሰንበታት ለዘለዓለም ለመኖር እንጣጣር፤ ጥረታችንን አምላክ ይመርቅልን። አሜን ወአሜን።